ABC FOUNDATION

ዓለምፀሐይ የጡት ካንሰር ፋውንዴሽን ምስረታ
Alemtsehay Breast Cancer Foundation (ABCF)
info@abcfonline.org * abcfonline.org
facebook.com/ABCancerFoundation

# የኢትዮጵያውያን የጡት ካንሰር ፋውንዴሽን በአትላንታ ተቋቋመ

ቅዳሜ፣ ሰኔ 15፣ ቀን 2013 ዓም በአትላንታ ከተማ "የዓለምፀሐይ የጡት ካንሰር ፋውንዴሽን" (Alemtsehay Breast Cancer Foundation) መመሥረቱን ወ/ሮ ፊፊ ደርሶ ለኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አስተዋውቀዋል። የፋውንዴሽኑም የመጀመርያ ስብሰባ የተደረገው በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማዕከል ነበር። በስብሰባው የተገኙት ተሳታፊዎች በአትላንታና በአካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ፣ ስለፋውንዴሽኑ መመስረት እጅግ መደሰታቸውንና ሙሉ በሙሉም ድጋፋቸውን የሚለግሱ መሆናቸውን ገልጸዋል። ከተሰበሰቡት መካከል 3ቱ ከካንሰር ህመም የዳኑ (survivors) መሆናቸውን ሲናገሩ፣ "ድርጅቱ አስፈላጊና ወቅታዊ መሆኑን አስረድተዋል። በዋና ተናጋሪነት የተጋበዙት ወ/ሮ ለምለም ጸጋው ከዋሽንግተን ዲሲ ነበሩ።

ፋውንዴሽኑ የሚቀጥሉትን አገልግሎቶች ለመሥጠት አቅዷል፤

1. በአሜሪካ ያሉ ኢትዮጵያውያን እንደ እድሜያቸው የሚደረገውን የጡት ምርመራ በራሳቸውና በሃኪሞች እንዲመረመሩ ማስገንዘብ፣ በሽታውም ይዟቸው በህክምናም ላይ ካሉ የመንፈስም ሆነ የገንዘብ ድጎማ እርዳታ መለገሥ፥
2. በአሜሪካ ለሚገኙ በጡት ካንሰር ለተያዙ ኢትዮጵያውያንና ቤተሰቦቻቸው ደጋፊ ማህበር (support group) ማቋቋም፥
3. በኢትዮጵያ ለሚኖሩ ሴቶች ስለበሽታው ምንነትና ምን ማድረግ እንድሚችሉ፥ ህክምናም ሆነ ትምህርት ስለበሽታው ሴቶችም ሆኑ ወንዶች እንዲያገኙ፣ ከጤና ባለሙያዎች ጋር በተለያዩ ሃኪም ቤቶችና የጤና ጣቢያዎች በመተባበር መሥራት፥
4. በአሜሪካ አገር ካንሰርን ለማጥፋት ለሚረባረቡ ድርጅቶች ስለኢትዮጵያውያን ሴቶች ለምርመራም ይሁን ህክምና ለማግኘት ያለባቸውን ችግር አስረድቶ ድጋፍ እንዲሰጡ መጣር፥
5. ስለጡት ካንሰር ጥናት የሚያደርጉትን ተቋማት በአሜሪካ የሚኖሩ በጡት ካንሰር የተያዙ ኢትዮጵያኖችን ቁጥር ለይተው እንዲመዘግቡ መገፋፋት።

ዓለምፀሐይ የጡት ካንሰር ፋውንዴሽን ምስረታ
Alemtsehay Breast Cancer Foundation (ABCF)
info@abcfonline.org * abcfonline.org
facebook.com/ABCancerFoundation

NEWS RELEASE, June 18, 2013

# A new Ethiopian breast cancer foundation formed in Atlanta

On Saturday, June 15, 2013, Ms. Fifi Derso, announced the creation of **Alemtsehay Breast Cancer Foundation** (ABCF) in Atlanta. In attendance were Ethiopian women in Atlanta and its surroundings. Three of the attendees were cancer survivors. At the end of the meeting all the participants welcomed the establishment of the foundation and pledged their support. The guest speaker was Ms. Lemlem Tsegaw from the Washington DC Metro Area.

**Alemtsehay Breast Cancer Foundation's objectives:**

Alemtsehay Breast Cancer Foundation (ABCF) is a nonprofit organization dedicated to help Ethiopian women worldwide who are burdened with financial need and strives to:

1. Encourage Ethiopian women to access available services for breast cancer screening, diagnosis, and treatment in their community;
2. Establish support groups for cancer patients, survivors and their families;
3. Guide Ethiopian women to optimal health through increased awareness about breast cancer;
4. Network with other organizations in the community to make them aware about the prevalence of breast cancer among Ethiopian women and seek help to alleviate their burden in obtaining screening and treatment services; and
5. Encourage and collaborate with breast cancer researchers in the U.S. to include the Ethiopian population in their surveys.